# በቅዠትና በስካር ጊዜ፣ ሁሉ በዕጅ ሁሉ በደጅ ይመስላል

ሙሉማር ኪሮስ (ከጎንደር)
mulumarkiros@gmail.com

ባለፈው ሳምንት «የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁና የ ጥልቅ ተሃድሶው የሰላም ቅብብሎሽ ይስመር ይሆን?›› የምትል ፅሁፍ ልኬ በአይጋ ፎረም በኩል ወጥታ ነበር፡፡ ለዚች ፅሁፍ መልስ ይሆን ዘንድ አቶ ሀብቱ የሚባሉ ፀሃፊ አሁንም በአይጋ ፎረም በኩል መልስ ልከውልኝ አነበብኩት፡፡ የዛሬ ፀሁፌ አላማ አቶ ሀብቱ (የአባታቸው ስምናከየት እንደሆኑ አልገለፁም) በላኩልኝ መልስ ላይ የራሴን አስተያየት ለመስጠት ነው፡፡

በመጀመሪያ አቶ ሀብቱ ፅሁፌን በማንበባቸውና ከዛም አልፈው ጊዜ ሰጥተው ለፅሁፌ የሚሆን መልስ በመስጠታቸው በጣም ደስ ብሎኛል፤ ሳላመሰግናቸውም አላልፍም፡፡ እኔ የላኳትን ፅሁፍ በውስጤ ያለውን ፍርሃትና ስሜት ለመግፅ እንጂ ፓለቲከኛ ሆኜ ወይም የፓለቲካ ድርጅት አባል ሆኜም አይደለም፡፡ እንደ ተራ ዜጋና ነዋሪ በትግራይ ተወላጆች ላይ የደረሰብንን አስፈሪና እኛን ለማሸማቀቅ የተደረገው ድርጊትና ፍፃሜ እንዲሁም ለስራ ጉዳይ በአንዳንድ የክልሉ መንግስት መስሪቤቶች ስሄድ የማየውና የምገነዘበው ነገር ስላላማረኝ ነው፡፡ ከቀባሪ ወድያ ማን ያርዳ ነውና ብዕሬን ለማንሳት ተገፋፋሁ፡፡ ያም ሆኖ ከአቶ ሀብቱ ፅሁፍ ጋር ከ 50 በመቶ በላይ እስማማለሁ በተለይም ስለ አማራና የትግራይ ህዝብ ለዘመናት የዘለቀ ቁርኝትና ወዳጅነት እንዲሁም የትግራይ ህዝብና አብዛኛው የብአዴን አባላት ያለው ፍቅርና ህዝባዊ ትስስር ከፍተኛ እንደሆነ አምናለሁ፡፡ ለዚህም አክብሮት እሰጣለሁ፡፡

ለመግቢያ ይህ ካልኩኝ በኂላ ከዚህ በታች ላሉት የአቶ ሀብቱ ግራ ቢስ መልሶች ግን የራሴን አስተያየት እንደሚከተለው አቀርባለሁ፡፡

ሀ) አቶ ሀብቱ በፅሁፋቸው ያነሱት የትግራይ ተወላጆች ከጎንደር ሲባረሩ ነፃ የአውሮፕላን ትኬት ተዘጋጅቶላቸው ነበር ብለዋል፡፡ በራሳቸው አንደበት እንዲህ ነበር ያስቀመጡት “Most of the Tigrians from Gonder were given a choice of transportation including free airlines ticket and were asked whether they want to go to Axum, Mekelle or Addis Ababa”. የሚል ነው፡፡ ማሽላ እያረረ ይስቃል አሉ፡፡ በዚህ ንግግራቸው እኔንም አሳቀኝ፡፡ በሳቸው አባባል ግፍ የደረሰባቸው ወገኖች ነፃ የአውሮፕላን ጉዞ ተዘጋጅቶ ወደ አክሱም ወይም መቀሌ ሂዱ ሲባሉ አንፈልግም ብለው ነው ልጆቻቸውና በእድሜ የገፉ ኣረጋውያን ተሸክመው ለቀናት ከተጓዙ በኋላ በረሃብና በእንግልት ሱዳን የገቡት፡፡ አሁን ለዚህ አይነቱ የአቶ ሀብቱ ሃሳብ ምኑ መልስ ይሰጣል፤ ስለሆነም ትቼዋለሁ፡፡ ነገር ግን ለአቶ ሀብቱ አንድ ሁለት የሚሆኑ ጥያቄዎች ላንሳባቸው፡፡ አንደኛ የትኬቱ ወጪ ሊሸፍን የነበረው ማን ነበር? የአንድ ትንሽ ከተማን የሚያክል ከ 7500 በላይ የሚሆኑ ወገኖች ከጎንደር ወደ አክሱምና መቀሌ ለማጓጓዝ ስታስቡ የኢትዮጵያ አየር መንገድስ የትኞቹ አውሮፕላኖች ነበር ያዘጋጀው?

ነው ወይስ የኢሜሬትስ አየር መንገድ ነበር ያዘጋጃችሁት? ሌላው ደግሞ ምነው ለቅማንት ወንድሞቻችንስ እንደዚህ አይነቱ ዕድል ነፈጋችኋቸው?

ለ) ሁለተኛው በአቶ ሀብቱ ፅሁፍ የተነሳው የትግራይ ተወላጆች መባረር የሚያስገርም አይደለም ይሉናል ምክንያቱም በሳቸው አባባል ካሁን ቀደም የአማራ ወገኖችም ከደቡብ ህዝቦችና ቤንሻንጉል ክልሎች ተባረዋል ብሏል። ይህ ሃሳብ ብዙ በብአዴን ውስጥ የመሸጉ ባህታዊ መነኩሴዎችና አፈቀላጤዎቻቸው የሚያነሱት ሃሳብም ነው። ከሳምንታት በፊት በዚሁ በአይጋፎረም በኩል አቶ እውነቱ ዘለቀ (የብአዴን አመራር እንደሆኑ የገለጹት) አቶ ሲሳይ አዲሱ (አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የመሸጉ) እና አቶ ተኮላ መኮንን የተባሉ ፀሃፊዎች እንዲህ ብለው ነበር። የአማራ ወገኖችን ከአንዴም ሁለቴ በግፍ ተባረዋል እናም የትግራይ ተወላጆች ከጎንደር ቢባረሩ ምን አዲስ ነገር መጣ? ተባረሩ እናስ ምን ይጠበስ? ብሏል። ይህን በተለመከተ አቶ እውነቱ ዘለቀ የተባሉት ‹‹ወጥ ረገጣችሁ ሲሉ›› አቶ ተኮላ መኮንን የትኛው የአማራ ተወላጅ በክልላችሁ አለና ነው አማራን አክብራችሁ ያኖራችሁት ብለዋል። የትግራይ ህዝብ የአማራ ወገኑን ለማፈናቀል ፍጹም ባያስብም በአቶ ተኮላ አነጋገር ግን ማባረር ብትፈልጉ እንኳ የትኛው አማራ እንዳታባርሩ ነው የሚል ድምጽ ያዘለ ነው። ቃል በቃልም ‹‹ለዩኒቨርስቲ ትምህርት የሄደን ተማሪ ካልሆነ በስተቀር›› ብሏል።

እርግጥ ነው በአማራ ብሄር ተወላጆች የደረሰውን በደል ከመጠን በላይ ያሳዝናል። ሁላችንም አዝነናል። ነገር ግን በጉራፈርዳና በቤኔሻንጉል አካባቢ በአማራ ክልል ተወላጆች የደረሰውን በደል ሂሳቡ የሚያወራርደው የትግራይ ህዝብ ነው እንዴ? በየትኛው ዕዳው? ደግሞስ የአማራ ተወላጆች በጉራፈርዳና በቤንሻንጉል ሄደው የአካባቢውን ለም መሬት ይዘው ተስፋፍተው ሲያርሱ የአካባቢው ወገኖች የሚያርሱት መሬት አጥተው ችጋር ሲገርፋቸው ከአማራ ወገኖቻቸው ጋር ግጭት ቢፈጥሩ የነሱ ስህተት ምኑ ላይ ነው? ስህተቱ የተፈጠረው የአካባቢው መንግስት አስተዳዳሪዎች ይህንን ችግር ሊፈጠር እንደሚችል ተገንዝበው በቅድሚያ መስራት የነበረባቸው ባለመስራታቸው ነው። እናም አቶ ሀብቱ ወደኛው እንመለስና የትኛው የትግራይ ተወላጅ ነው ጎንደር መጥቶ ለም መሬቱ ላይ ተንሰራፍቶ የተገኘውና ለመባረር የበቃው? በከተማ ውስጥ ሰርቶ የሚኖረው የትግራይ ተወላጅ አይደለም እንዴ ያበራራችሁት? ይህም አልበቃ ብሎ ትግረኛ ተናጋሪ የሆኑትን የበረንዳ አዳሪዎችና ድሆች ይዛችሁ ስታበቁ ጎንደርን ሊያቃጥሉ የያዝናቸው የወያኔ ቅጥረኞች ብላችሁ አይደለም እንዴ ድፍን ጎንደርን ሰብስባችሁ ‹‹ጉሮ ወሸባዬ›› ያላችሁት? በነጋታው ሚስኪን ድሆች መሆናቸውን አረጋግጦ ፖሊስ ፈታቸው። ይህ አያሳፍርም!

ደግሞስ እነ አቶ ሀብቱ አዙሮ የሚያይ አንገት የላችሁም እንጂ የአማራ ገዥ መደቦች ህልቆ መሳፍርት በሌላው ግፍ በተለያየ የአገራችን ህዝቦች ባደረሱት በደል ምክንያት ግፍ የደረሰባቸው ህዝቦች (ማህበረሰቦች) በአማራ ህዝብ ላይ ለበቀል ሲዘጋጁ የትግራይ ህዝብና ህወሐት (ወያኔ) ግን ቂምና ቁርሾ እንዲቀርና የአገራችን ህዝቦች በስምምነትና በፍቅር አዲሲቷን ኢትዮጵያ

ለመመስረት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡ ይሄንንስ ረሳችሁት? አሁን ያለው የአገራችን ሰላም ቢበላሽ የመጀመሪያ ተጎጂ ማን የሚሆን ይመስልዎታል?

ሐ) ሌላው አቶ ሀብቱ የተቃወሙት ጉዳይ በጎንደርና አካባቢው ሙሉ በሙሉ የተሃድሰው የሰላም ውጤት እስኪታይ ድረስ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ቢያንስ በጎንደር አካባቢ ይራዘምልን ማለቴን ነው፡፡ በእሳቸው አባባል ከሆነ ከተራዘመም በሃገሪቱ ሙሉ ይራዘም እንጂ በጎንደር አካባቢ ተለይቶ ማራዘሙ ‹‹በቁስል ላይ ጨውን መነስነስ እንደ ማለት ነው›› ብሏል፡፡

በኔ እምነት ግን ሲጀመር መንግስት እንዲህ አይነት በድፍን አገር የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ማወጁ በብዙ መልኩ ሲታይ ተገቢ አልነበረም፡፡ ምክንያቱም ችግሩ የታየው በኦሮሚያ፣ በአማራና፤ በአንድ ከተማ (ዲላ) ደግሞ በደቡብ ህዝቦች ክልል ውስጥ ነው፡፡ ሌሎቹ ስድስት ክልሎች፣ ሁለቱ የፌደራል ከተማ አስተዳደሮች፤ እንዲሁም ከ95 በመቶ በላይ የደቡብ ህዝቦች ክልሎች ሰላም ነበሩ፡፡ በመሆኑም እነዚህ በሰላም የነበሩት ክልሎች ወደዚህ አዋጅ መካተታቸው ለአጃቢነት ተብሎ የተደረገ ካልሆነ በስተቀር ጥቅሙ አይታየኝም፡፡ እዚህ ውስጥ በመካተታቸው ግን ለአገሪቷም የክልሎቹም ኢኮኖሚ አሉታዊ ተፅእኖ አሳድ[ል፡፡

ሁለተኛው ቁም ነገር ወደድንም ጠላንም በጎንደር አካባቢ ያለው ሰላም አስተማማኝነቱ መታየት ያለበት በጊዜ ሂደት ነው፡፡ የውጭና የውስጥ ጠላቶች መናሃሪያቸውና አውደ ግነባራቸው አድርገው እየተንቀሳቀሱበት ያለ አካባቢ ነው፡፡ ስለዚህ ሜጋ ፕሮጀክታችን በተለይም የህዳሴ ግድባችን የመጀመሪው ምዕራፍ እስኪጠናቀቅ ድረስ በዚህ አካባቢ ላይ አካሄዳችን ጥንቃቄ የተሞላበት መሆን እንዳለበት አምናለሁ፡፡

በተጨማሪም በአሁኑ ሰዓት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ አስፈፃሚው ኮማንድ ፖስት በአማራ ክልል ለተፈፀሙ ግፎች የትኛው የብአዴን አመራርና አባል ምን ተራ ነበራቸው የሚሉ በእጁ የገቡ ብዙ ማስረጃዎች ይገባሉ ብዬ አምናለሁ፡፡ ለብአዴን ጥልቅ ተሃድሶም እነዚህ መረጃዎች ወሳኝ ግብአቶች እንደሚሆኑ እገነዘባለሁ፡፡ በዚህም መሰረት ኢህአዴግ የብአዴን ክንፉ ማጥራትና ማስተካከል ይገባዋል፡፡ ይህ ሊታለፍ የማይገባው ኢህአዴግን የማደስ መልካም አጋጣሚ ነው፡፡ በመሆኑም እነዚህ ነገሮች እስኪስተካከሉና አስተማማኝ የሆነ ሰላም እስኪረጋገጥ ድረስ እዚህ አከባቢ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን ቢራዘም ለሁሉም ጠቃሚ ነው፡፡

መ) አቶ ሀብቱ ሌላ ያነሱት ሀሳብ ‹‹ጥቂት የትግራይ ተወላጆች የአከባቢውን ህዝብና ባህሉ ሳያከብሩ በፖሊስና በመከላከያ ሀይል ከለላ ተሰጥቷቸው መኖርን ይፈልጋሉ ብሏል፡፡ እኔ ግን እንዲህ አይነት እምነት ያለው የትግራይ ሰው አላጋጠመኝም፡፡ እኔ በበኩሌም እንዲህ ዓይነት እምነት የለኝም፡፡ ቢፈለግ እንኳን አይቻልም፡፡ ምክንያቱም የአካባቢውን ህዝብ፣ ባህሉና የሀገሪቱ ህግ ለማያከብሩ ሰዎች ከለላ የሚሰጥ የመከላከያም ይሁን የፖሊስ ሀይል አሁን በኢትዮጵያችን የለም፡፡ ለዚህም ነው የሀገሩ ህዝብና ባህሉን አክብረን በሰላም ስንኖር የነበርነው፡፡

ሥ) ሌላው ጉዳይ በህዝቡ ላይ አይውሉ ውለው እና ምን ይጠበስ እያሉ ይቅርታም በአግባቡ ሳይከውኑ ነገሩን አታንሱት፣ እርሱት ይሉናል አቶ ሀብቱና መሰሎቻቸው:: ብንረሳው እኛም በወደድን፣ ግን በምን መልኩ? ብዙ ሞተዋል፣ ንብረቶቻቸውን ወድሟል፣ አሁንም ዜጎቹ በመላ ትግራይ በየቤተክርስትያኑና በረንዳው ወድቀዋል:: ይህ ብቻም አይደለም ለነዛ ሁሉ ተጠ ያቂዎቹ አሁንም በቦታቸው አሉ:: «ተሃድሶ» ተብሎ የተነሱት የክልሉ የቢሮ ሀላፊዎች ናቸው:: እነዚህ ሰዎች አብዛኛዎቹ የድርጅቱ ብአዴን ፕሮግራም ተቀብለውና አባልም ሆነው ሲያበቁ የሃገሪቱ ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አስፈፃሚ ባለሙያዎች ናቸው:: በመሆኑም ለተፈፀመው ግፍ አነዚህ ባለሙያዎች ተጠያቂ ነበሩ ለማለት አይቻልም። በህዝቡ ውስጥ ተሸሽገው ችግር ሲፈጥሩ የነበሩት ከወረዳ እስከ ክልል የነበሩ የህዝብ አስተዳዳሪዎች፣ የፀጥታ አደረ±ጀቶች፣ በየደረ±ው ያሉ የድርጅቱ (ብአዴን) የፕሮፖጋንዳና የድርጅት ጉዳዮች፣ የህዝብና ማህበራት አደረ±ጀቶች፣ ወዘተ ናቸው:: እነዚህ በሙሉ በቦታው አሉ ጥቂት የተዛወሩትም ለተሻለ ቦታ ነው:: በመሆኑም የወጋ ቢረሳም የተወጋ ሊረሳ አይችልም::

የትግራይ ህዝብ ልበ ሰፊና ይቅር ባይ ህዝብ ነው:: የሚፈልገውም ሰላምና እኩልነትን ነው:: በአሁኑ ጊዜም እነደ አጥር፣ እንደ ቅጥር ሆኖ በከፍተኛ የሃላፊነት መንፈስ ሀገሩንና ወገኑን ከድህነት ወጥተው ከቀደሙት ሀገራት ተርታ ለማሰለፍ ከሌላው ኢትዮጵያዊ ወገኑ በመትጋት ላይ ያለ ህዝብ ነው:: ይህ ህዝብ ከዚህ አይነት ትግል መውጣት አይፈልግም:: አሁን ብቻውንም አይደለም:: እሱን ለማጥቃት ስትሉ የምትጣሉትም ከመላ የኢትዮጵያ ህዝብ መሆኑን ተገንዝባችሁ አደብ ግዙ::

ስለዚህ ልክን ማውቅ ከራስ ጋር መታረቅ እንዲሉ እነ ተኩላዎች ከስካራችሁና ቅዠታችሁ ንቁ:: ተናካሽ ውሾቻችሁና ተዋጊ በሬዎቻችሁ እሰሩ፣ ህዝቡን ከልብ ይቅርታ ጠይቁ፣ የበደላችሁትን ህዝብ እንደምትክሱ ቃል ግቡ:: ይህ ነው የወቅቱ ተሃድሶ:: ቢከማች እዳው ላንች ነውና ጉዞውን በጊዜ ጀምሩት:: አለበለዚያ ያን ስትጭሩ ያም ስትጭሩ «መጫር ያበዛች ዶሮ የመታረ±ዋን ካራ ታወጣለች» እንዳይሆን መጠንቀቅ ብልህነት ነው::

ቸር እንሰንብት